# አጥፍቶ የመልማት ሕወሃታዊ ሴራ

(ተበጀ ሞላ)

ሕወሃት ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለው የበላይነት ጥያቄ ዉስጥ ከገባ የራሱን 'ሪፐብሊክ' ለመመስረት ዝግጁ መሆኑ ግልፅ ነው። አምስት ማሳያወችን ልጥቀስ፦

፩) ድርጅቱ ከምስረታው ማግስት ጀምሮ ዓላማው የራሱ ያላትን ዘውጋዊ መንግስት መፍጠር መሆኑን አሳውቋል (የድርግጅቱን ማንፌስቶ ልብ ይሏል)። ማዕከላዊ መንግስት ከመሰረቱም ቡሏላ ቁንጮ የሕወሃት ሰዎች በተለያየ አጋጣሚ የራሳቸውን ሃገር የመገንባት ህልማቸውን ዕውን ለማድረግ ያላቸውን ቁርጠኝነት ያለማመንታት ግልጽ ኣድርገዋል።

፪) እስከተቻለ ድርስ "እኛ ከሌለን ኢትዮጵያ አትኖርም" በሚል ማስፈራርያ አናሳውን ቡድን ብቻ ተጠቃሚ የሚያደርገውን ስርዓት ማስቀጠል፤ ካልተቻለ ድግሞ የወደፊቷን ዘውጋዊ ሪፐብሊክ የበላይነት ለማረጋገጥ ቀሪውን የኢትዮጵያ ክፍል በማያቋርጥ ብጥብጥ ዉስጥ ኣስገብቶ መውጣት እንደ ስትራቴጂ የተያዘ ይመስለኛል። ለዚህ ደግሞ ኣስፈላጊው ስራ ተሰርቷል። ኦሮሞ እና አማራ ኣዲስ አበባ ላይ ይፋጠጣሉ፤ ሶማሊ እና ኦሮሞ በምስራቁ ክፍል ይፋለማሉ፤ሲዳማው ትንሽ ሃገር ለመሆን ጦሩን ይሰብቃል፤ ፍጥጫው ዘርፈ-ብዙ ነው። ሕወሃቶች ህልማቸው በዚህ ሁሉ መሃል የሰላም ኣስከባሪነትን ሚና ይዘው የጠሉትን መቅጣት የወደዱትን መርዳት ይሆናል።

፫) የታሰበችውን ሪፐብሊክ በግብርና እና በኢንዱስትሪ ምርትራሷን ለማቻል ኣስፈላጊው ዝግጅትአየተደረገ ነው። ተራራማዋ የትግራይ ሪፐብሊክ እራሷን መመገብ እንድትችል ሰፋፊ ለም የርሻ መሬቶች ከወዲሁ በዘረፋ ተወስደዋል (ከወሎ ራያ፣ ከጎንደር ወልቃይት ወደ ትግራይ የተወሰዱት ይህንኑ ራዕይ እውን ለማድረግ ነው)። በኢንዱስትሪው እና አገልግሎት ዘርፉም ቀሪውን ያገሪቱ ክፍል የበይ ተመልካች ባደረገ መልኩ ግንባታው ቀጥሏል። (ሃገራዊ መስመር ላለው መንግስት ይህ አይነቱ አሰራር ከፍትሃዊ የልማት ተደራሽነት ጋር ተያይዞ የሚነሳ ጥያቄ በሆነ ነበር። እንዳለመታደል ሆኖ መስመራቸው ሃገራዊ አልሆነም።)

፬) ለያዙት የፖለቲካ የበላይነት እንዲሁም ነገ ለሚመሰርቷት ሪፐብሊካቸው እንቅፋት ይሆንብናል ባሉት የአማራ ህዝብ ላይ መጠነ ሰፊ ጥቃት ማካሄድ ከጀመሩ ፵ ዓመት አልፏቸዋል። ጥቃቱ ስነልቦናዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖማዊ ነው። በጥንቃቄ በተዘጋጀ መዋቅራዊ መሳርያ አማራውን የማሽማቀቅ፣ የማግለል፣ የማጥላላት እና የማቆርቆዝ ሥራ ተሰርቷል፣ እየተሰራም ነው። ከምንም በላይ ደግሞ አማራው አንደ ህዝብ ባንድ ላይ ቆሞ ጥቅሙን ማስከበር እንዳይችል በዉስጡ በየተኛውም ያገሪቱ ክፍል ባልታየ መልኩ "ልዩ ዞን" በሚል ስልታዊ እርምጃ በሁሉም አቅጣጫ (በወሎ፣ በጎንደር እና በጎጃም) ሽምቅ መዋግያ ምሽግ ተቆፍሮለታል። (ልብ እንበል: በትግራይ ክልል የሚገኙ ከ ፭ በላይ ዘውጎች እንኳን ልዩ ዞን ልዩ ቀበሌ የሚል እውቅና ኣልተሰጣቸውም።) ህወሓት ለቅማንት ማንነት መቀሌ ቢሮ ከፍቶ የሚታገለው ለነፍሱ አይደለም። 'ታሪካዊ ጥላቴ' ብሎ የፈረጀውን ሕዝብ በጅ አዙር ማጥቃቱ ነው። ስሌቱ ግልጽ ነው። በዉስጡ ተስፋፊ ጎሳዎች የተፈጠሩበት ህዝብ ከውጭ ለሚሰነዘር ጥቃት ምላሽ የመስጠት አቅሙ ዉስን ነው። በመሆኑም በነሱ እሳቤ አዲሷ 'ሪፔብሊክ' ተከዜን ተሻግራ፣ ራያ ወርዳ ለያዘችው መሬት ጠያቂ አይኖርም።

፭) በመጨረሻም፣ ሕወሃቶች የነገዋን nation-state ኢኮኖሚያዊ ዋስትና ለማረጋገጥ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሃብት ክምችት ያዩባቸውን ያገሪቱ ክፍሎች በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ

የሚያስችላቸውን  የቤት ስራ አጠናቀዋል ። ከሰሞኑ ብቅ ብሎ የጠፋው ትግራይን ከቤንሻንጉል ክልል ጋር የሚያገናኝ ካርታ እንደተባለው በተራ ስሕተት የተላለፈ ሳይሆን ታስቦበት የቀረበ ማስጠንቀቅያ ይመስላል  (፩ኛ ደረጃ ትምርቴን የጨረስኩት በትግራይ ክልል በመሆኑ ለዚህ ካርታ አዲስ አይደለሁም)። ሕወሃቶች ወደ ባህር የቀረበውን የአፋር አካባቢ በቀጥታ ለመቆጣጠር መቋመጣቸው ያለ ምክኒያት ነው ብሎ ለማሰብ ሞኝ መሆን አለብን። ተከዜን ተሻግረው አልማቀፍ ድንበር ማበጀታቸውም ሱዳን ናፍቋቸው አይመስለኝም።
ባጭሩ የሰዎቹ Plan B አጥፍቶ መልማት ነው። ለዚህ እቅድ ምላሹ አብሮ መልማትን መዳረሻው ያደረገ ፖለቲካዊ አሰላለፍ ነው። በተለይ ሁለት ነጥቦችን ላንሳ፣

(1) የትግራይን ሕዝብ እና ሕወሃትን እንለይ

ብዙዎች እንደሚስማሙት ያለ ትግራይ ኢትዮጵያዊነት ጎዶሎ ነው፤ ነፍስ የለውም። ስለሆነም ሃገራዊ ብሔርተኝነትን ማዕከል ያደርገ ፖለቲካ የትግራይን ሕዝብ ያቀፈ መሆን ይኖርበታል። ይህን ማድረግ ስትራተጂ ጠቀሜታም አለው፤ ከቀሪው ያገሪቱ ክፍል ጋር መተማመንን ከፈጠረ የትግራይ ሕዝብ ለሕወሃት መሰሪ ፕሮፓጋንዳ  በቀላሉ እጅ አይሰጥም። ያ ማለት ደግሞ ቡድኑ ከነወንጀሉ የሚደበቅበትን ዋሻ ዘጋን ማለት ነው። በርግጥ ለግዜው ይህ ሰነፍ ተስፋ ሊመስል ይችላል፤ ሆኖም ለዘመናት በክፉም በደጉም አብሮ ለኖረ ሕዝብ አሁን የተፈጠረን ጥመት በሂደት ማረቅ አይገደውም።

(2) የዜግነት  ፖለቲካ አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር በዘውግ እና በዜግነት ስበት
የተቃኘ ነው።  ሃገራዊ  ብሄርተኝነት መሰረቱ ዜግነት ነው። ትኩረቱም ወደፊት ነው። ታሪክን የጋራ ድልን ለማሰብ ይጠቀምበታል። ያለፈን በደልን ሳይረሳ እንዳይደገም  ያላሰለሰ  ጥረት ያደርጋል።  እንደ ነፃነት እና ፍትህን ለመሰሉ አለማቀፋዊ እሴቶች ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣል። ከምንም በላይ ደግሞ ገለሰብ በራሱ ሙሉ ነው።

በተቃራኒው ዘዉጋዊ ብሄርተኝነት መሰረቱ ቡድን ነው። ከግለሰብ መብት ይልቅ ለመንጋ ጥያቄ ቅድምያ ይሰጣል። ታሪክን የበዳይ እና የተበዳይ ትግል ብቻ አድርጎ ይወስዳል። በዚህም ምክንያት 'የኔ' የሚለው ቡድን ሕልዉና የሚረጋገጠው 'ጠላቱ' የሚለው ቡድን ላያንሰራራ ሲወድቅ ብቻ ነው። የዘውግ ብሄርተኝነት በተፈጥሮው ተስፋፊም  ነው። አይኑ ያረፈበትን ሁሉ የራሱ ለማድረግ አዲስ ታሪክ በዘመቻ ያፅፋል፣ ያስተምራል።

በዛሬዋ ኢትዮጵያ፣ ዘዉጋዉያን ከመሃል ሃገራዊ ብሄርተኞች ከዳርቻ  የፖለቲካ ገመድ ይጓተታሉ። በኔ እምነት ኢትዮጵያዊነትን  ሕወሃት ከደገሰለት ጥፋት መታደግ  የሚቻለው የዜግነት ፖለቲካ ከዳር ወደ መሃል ሲዘልቅ እና የተዘራውን የመፈራራት፣ የመጠራጠር መርዝ ማርከስ ሲችል ብቻ ነው።

እንደ ኢትዮጵያ ላለ ሕብረ-ብሔር የፖለቲካ ማህበርሰብ ዘዉግ-ተኮር ፖለቲካ አያዋጣንም ሲባል የዘውግ ፖለቲካ በባህሪው አግላይ በመሆኑ ነው። ከዚያም  አልፎ ሆን ተብሎ ሲጦዝ ወደ እብሪትና የከፋ ጦርነት ያስገባል። ያለ ያለ ጀርመን ብሄርተኝነት ሁለቱ ያለም ጦርነቶች አይታሰቡም፣ ብሄርተኝነትን ሳያቀነቅኑ ሞሶሎንም ሆነ ቶጆ በጣልያን እና ጃፓን ህዝቦች ስም ዘግናኝ ግፍ ባልፈፀሙ ነበር።

ከዚህ አንፃር የዘውግ ማንነት ከመጠን በላይ ሲገዝፍ የሚያመጣውን አደጋ ቀድመው የተረዱት ቻይናወች የኮንፈሽያን እና ዳኦይስት አስተሳሰብን የጋራ እሴት በማድረግ ባገሪቱ የሚገኙ ጎሳወች ዜግነትን መሰረት ባደረገ ሃገራዊ ማንነት  ስር እንዲሰባሰቡ ጥረት ከጀመሩ ሰንብተዋል። የኛዎቹ ጉዶች የልማታዊ መንግስትን ፅንሰሃሳብ አመጣንባት  የሚሏት ሲንጋፖር በ40 ዓመት

**ዉስጥ ከወደብ ከተማነት ወደ አለማቀፋዊ የኢኮኖሚ ማዕከልነት የተሸጋገረችው የነበረውን አደገኛ የዘውግ ፍጥጫ በሀገራዊ ብሄርተኝነት በመተካት ትኩረቷን ሙሉበሙሉ ልማት ላይ በማድረጓ ነው።**

**ቸር ያሰማን።**


[**ኢትዮሚድያ** - Ethiomedia.com]

September 8, 2017